

**Amhara Association in The Netherlands**

**PRESS RELEASE**
**ጋዜጣዊ መግለጫ**
**FEB-MAR 2026**

# የዘር ጭፍጨፋ እየተፈጸመበት ላለው ለአማራ ህዝብ ድምጽ ለመሆን እንዲሁም ፈጻሚዎቹ ለፍርድ እንዲቀርቡ የሚጠይቅ ሰላማዊ ሰልፍ ተደርጓል




ማህበሩ ከአለም አቀፉ አማራ ማህበራት ህብረት ጋር በመተባበር በማርች 20 አርብ ቀን በ ዘ ሄግ ከተማ በውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ቢሮ በር ላይ የተሳካ ሰላምዊ ሰልፍ አድርጓል።

በሰልፉ ላይም በርካታ ተሳታፊዎች ተገኝተው ድምጻቸውን ያሰሙ ሲሆን ፕሮግራሙም በ ፍሪ ፕሬስ ኢትዮጵያ የዩትዩብ ቻናል የቀጥታ ስርጭት አግኝቶ በሺዎች ተመልክተውታል።

የአማራ ህዝብ ላይ እየተደረገ ያለው የዘር ጭፍጨፋ ይቁም ፥ ሴቶች እና ህጻናት ላይ የሚደረገው ጾታዊ ጥቃትን እንደ ጦር መሳሪያ የመጠቀም የጦር ወንጀል ይቁም ፥ በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ላይ የሚፈጸመው ግድያ ይቁም ፥ የአለም አቀፉ የጦር ወንጀለኞች ፍርድ ቤት የዘር ጨፍጫፊዎችን ለፍርድ ያቅርብ ፥ ከዚህ ዘር ጨፍጫፊ መንግስት ጋር የሚደረግ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ትብብር ይቁም ፥ ያለ ጥፋታቸው የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ እና ሌሎችም መፈክሮች የተሰሙ ሲሆን ማህበሩም ለኔዘርላንድ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት እነዚህን ጥያቄዎች የያዘ ደብዳቤ ማስገባቱን ለተካፋዮች አሳውቋል።












# ሊቆም ያልቻለው የአርሲ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት መሪዎች እና የምዕመናን ግድያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በእምነታዊ እሴቶች ፥ በኪነ ህንጻ ፥ ስነ ጥበብ ፥ ስነ ስዕል ፥ ዜማ ፥ ፊደል ፥ ትምህርት ፥ ስነ ምግባር ፥ ታሪክ እና ለትውልድ ነጻነትን በጀግንነት የማስከበር ታሪክ በማስተማር በወራሪ ያልተደፈረች ሃገር በማቆየት ከፍተኛ ተሳትፎና አረአያነት ያሳየች ባለውለታ ነች።




ነገር ግን ይህ የቤተክርስትያኗ ውለታ ተረስቶ ቅጥር ግቢዋ ተደፍሮ ምዕመኖቿ እና የሃይማኖት መሪዎቿ ሲገደሉ ማየት እና መስማት በጣም አሳዛኝ ሆኖ ማህበሩ አግኝቶታል።

በተለይም ባሳለፍነው ወር የካቲት በዞኑ ሽርካ ወረዳ ጃዊ ቀበሌ እና በሮቤ ወረዳ ገባ ቀበሌ በተፈጸመ ጥቃት ቁጥራቸው ከሰላሳ የሚልቅ ሰዎች መገደላቸውን፣ አካል ጉዳት መድረሱን፣ እገታ እና መፈናቀል ማጋጠሙን አማኔ ተረድቷል፤ በዚህም የድርጊቱን ፈጻሚዎቹን በማውገዝ የሃገር ውስጥ ህግ አስፈጻሚ አካላት ይህን የአገዛዙን እና በስፍራው ያሉ ታጣቂዎች ጭፍጨፋ በማውገዝ ለፍርድ እንዲያቀርቡ ማሳሰቢያ ሰጥቷል።






# Amhara Association in The Netherlands

## PRESS RELEASE
## ጋዜጣዊ መግለጫ
**FEB-MAR 2026**




# የአማራን አንድነት ማጠናከር ላይ ሊኖር የሚገባው የዲያስፖራው ተሳትፎን በሚመለከት አማኔ ከአባላት እና ደጋፊዎቹ ጋር በቨርችዋል ዙም ውይይት አድርጓል

ማርች 15 ማታ 19:30 ጀምሮ የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ በተጋባዥ እንግዶቹ ታጅቦ ከ25 በላይ ከሚሆኑ አባላት እና ደጋፊዎቹ ጋር የዙም ውይይት ያደረገ ሲሆን የውይይቱም አጀንዳዎች "**የአማራን አንድነት ለማጠናከር የዲያስፖራው ተሳትፎ ምን መሆን አለበት**" እንዲሁም "**የማህበሩ የወራት እቅዶች እና የተሰሩ ስራዎች**" ላይ ለሁለት ሰአታት ውይይት አድርጓል።

ከተጋባዥ እንግዶች አንዱ የሆነው የአለም አቀፉ የአማራ ማህበራት ህብረት ሰብሳቢ ኢ/ር ግርማ ባለፉት ሶስት አመታት የነበረውን የአማራ ዲያስፖራ እንቅስቃሴ በመዳሰስ እና በእንግሊዝ ሃገር ያለውን እንቅስቃሴ እንደ መነሻነት በመውሰድ ለአማኔ አባላት እንዲሁም ለደጋፊዎች መልዕክቶችን አስተላልፏል።

በዙም ውይይቱ ላይም ከአባላት የተነሱ በርከት ያሉ ጥያቄዎች የነበሩ ሲሆን ከነዛ ውስጥም አማኔ ከአባላቱ ጋር ስላለው ግንኙነት እና ከዚህም በላይ ጠንካራ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆነ ማህበር የሚሆንበትን አካሄድ የሚያመላክቱ ጥያቄዎች ተነስተዋል። ለዚህም መልስ የሰጡት የማህበሩ ሰብሳቢ ማህበሩ ብዙ ስራዎችን ለመስራት እቅድ ቢኖረውም በሰው እጥረት ምክንያት ያልጀመራቸው የስራ ክፍሎች እንዳሉ በተለይም የቋንቋ እና ስነጽሁፍ ክፍሎች ላይ ሰው እንደሚያስፈልግ ገልጸው ለተሰብሳቢውም ጥሪ አቅርበዋል።

ከአዳዲስ አባላት ምዝገባ ጋር በተያያዘም ማህበሩን በአባልነት ወይም በደጋፊነት መቀላቀል የሚፈልጉ በጎ ፍቃደኞች በማህበሩ ድህረ ገጽ በመግባት እንዲመዘገቡ እና ማህበሩን እንዲያግዙ ጥሪም ቀርቧል።



**Amhara Association in The Netherlands**

**PRESS RELEASE**
ጋዜጣዊ መግለጫ
**FEB-MAR 2026**

# ለአማራ የጦርነት ተጎጂዎች የሚውል የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም በየካቲት እና በመጋቢት ወራትም ቀጥሏል

በአማራ ህዝብ ላይ እየተደረገ ያለው ስልታዊ የዘር ጭፍጨፋ ከተጀመረ ከሶስት አስርት አመታት በላይ መቆጥሩ ይታወቃል። አሁን ባለንበት አምስት አመታት ውስጥ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ጦርነት ታውጆበት በመቶ ሺዎች ለሞት ፥ በሚሊዮኖች ከቀያቸው ለማፈናቀል እና ለሰው ሰራሽ ረሀብ እንዲሁም ከ አምስት ሚሊዮን በላይ ህጻናት እና ወጣቶችን ደግሞ ከትምህርት ገበታቸው ላይ እንዳይገኙ አድርጓል።




ለነዚህም ተጎጂዎች መሰረታዊ የምግብ ፥ የንጽህና መጠበቂያ ፥ የመድሃኒት እና የአልባሳት እረዳታ ማድረግ እንዲቻል ይረዳ ዘንድ ከዚህ ቀደም በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደተደረገው የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ የገቢ ማሰባሰቢያ መንገድ አዘጋጅቶ እንቅስቃሴ ከጀመረ ከሁለት ወራት በላይ ተቆጥረዋል።

በየካቲት ወር ላይም የማህበሩ የአመራር አባላት በተገኙባቸው ፕሮግራሞች ላይ ለገቢ ማሰባሰቢያ የተዘጋጀውን በራሪ ወረቀት በመበተን እና የማህበሩን አላማም በማስረዳት ከተለያዩ የሃሳቡ ደጋፊ ኢትዮጵያውያን የተወሰነ ድጋፍ ማግኘት ተችሏል።

ይህ በጎ ሃሳብ እና ጅማሮ ተጠናክሮ መቀጠል ስላለበት እርስዎም ከአንዲት ዩሮ ጀምሮ አቅማችሁ እስከቻለው ድረስ በአማራ ማህበር በኔዘርላንድ የባንክ አካውንት ማለትም “**Vereniging van Amharas in Nederland**” “**NL07 INGB 0108 1617 81**” በሚያስገቡበትም ግዜ የመላኪያ ምክንያት ላይ “**INK_NOODFONDS**” የሚለውን መለያ (betalingskenmerk / reference) በመጨመር ቢልኩ ማህበሩም የተቀበልነውን አደራ ለተጎጂዎች ወገኖቻችን በማድረስ የቆመበትን አላማ እና ግዴታዎቹን እንደሚወጣ ገልጿል።